## ትምህርት አንድ፡- አጋዥ መሳሪያዎች ምንድን ናቸው?

- አጋዥ መሳሪያዎች ማለት በጥሩ ሁኔታ ወይም ከነጭራሹ ተግባራትን ለማከናወን የሚቸገሩ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ናቸው።
- አጋዥ መሳሪያዎች በልጆች እና አዋቂዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።
- ሰዎችን በተለያዩ የህይወት አካባቢዎች የሚያግዟቸው በርካታ የአጋዥ መሳሪያ አሉ፣ ለምሳሌ፡- ለማሰብ፣ ለተግባቦት፣ ለመስማት፣ ለመመልከት፣ በዙሪያ ለመንቀሳቀስ እና ራስን ለመንከባከብ የሚያግዙ ናቸው።
- በርካታ ሰዎች በፍላጎታቸው ላይ በመመስረት ከአንድ በላይ አጋዥ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ።

## ትምህርት ሁለት፡- አጋዥ መሳሪያዎችን ለማቅረብ ማን ይሳተፋል?

- በርካታ ሰዎች የሚከተሉትን ጨምሮ የአጋዥ መሳሪያዎችን ለማቅረብ የሚጫወቱት ሚና አላቸው፡-
  - አጋዥ መሳሪያ የሚፈልገው ግለሰብ
  - ቤተሰቦቻቸው እና ጓደኞቻቸው
  - አጋዥ መሳሪያዎች የሚፈልጉትን ወደ አገልግሎት የሚጠቁሙ ሰዎች
  - የሰለጠኑ የአገልግሎት ሰጪዎች
  - በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች

## ትምህርት ሶስት፡- እንዴት አጋዥ መሳሪያዎች እንደሚቀርቡ

አጋዥ መሳሪያዎች በ 4 እርምጃዎች ይቀርባሉ፡-




- መሳሪያው አሁንም ፍላጎቶችን እያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ እነዚህ አራት እርምጃዎች ሰዎች ደህንነታቸው በተጠበቀ፣ አግባብነት ባላቸው የአጋዥ መሳሪያዎች እንዳገኙ፤ የሚጠቀሙባቸውን ክህሎቶች እንደያዙ እና መሳሪያው አሁንም የእነርሱን ፍላጎቶች እንዳሟላ ለማረጋገጥ እነሱ የክትትል እገዛ እያገኙ መሆኑን ያግዛል።
- መሳሪያውን የሚቀበለው ግለሰብ (እና አግባብነት ሲኖረው ቤተሰቡ ወይም እንክብካቤ ሰጪው) በእያንዳንዱ የሂደት ደረጃ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆኑ አስፈላጊ ነው።

## ትምህርት አራት፡- በአጋዥ መሳሪያ የአገልግሎት አቅርቦት ውስጥ ከግምት ውስጥ የሚገቡ ነገሮች

- አንዳንድ አጋዥ መሳሪያዎች ለማቅረብ በርካታ ጊዜ ይፈጃሉ - ሌሎቹ ደግሞ በፍጥነት ሊቀርቡ ይችላሉ። ይህ በተለያዩ ምክን ያቶች ላይ ይመሰረታል፣ ይህም የሚያካትተው፡-
    - አጋዥ መሳሪያው ምን ያህል ውስብስብ (የተወሳሰበ) እንደሆነ
    - የግለሰቡ ፍላጎቶች እና የጤና ሁኔታዎች
    - ግለሰቡ አጋዥ መሳሪያውን የሚጠቀምበት አካባቢ
    - መሳሪያውን የሚጠቀመው ግለሰብ ምን ያህል ልምድ ያለው እንደሆነ።
- በትክክለኛው አጋዥ መሳሪያ እንኳን፣ ሰዎች ብዙ ጊዜ ማድረግ የሚፈልጓቸውን ነገሮች ለማድረግ ተግዳሮቶች ይገጥሟቸዋል። እነዚህ ተግዳሮቶች ሊያካትቱ የሚችሉት፡-
    - ተደራሽ ያልሆነ አካባቢን የመሰሉ ተግዳሮቶች
    - መገለል እና መድልዎ
    - ተደራሽ የሆነ መረጃ እጥረት
    - የድጋፍ ፖሊሲዎች እና አገልግሎቶች እጥረት
- አጋዥ መሳሪያዎችን የሚጠቀሙ ሰዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ እና ማድረግ የሚፈልጓቸውን ነገሮች እንደሌሎች በእኩል ደረጃ ማድረግ መቻላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ሁሉም ሰው ሚና አለው።